# ትንቢተ አብድዩ

1የአብድዩ ራእይ፤
ጌታ እግዚአብሔር ስለ ኤዶም እንዲህ
ይላል፤
ከእግዚአብሔር ዘንድ መልእክት
ሰምተናል፤
መልእክተኛውም ወደ አሕዛብ ተልኮ እንዲህ
ብሎአል፤
“ተነሡ፤ እርሷን ለመውጋት እንውጣ::”
2“እነሆ፤ በአሕዛብ መካከል ታናሽ
አደርግሃለሁ፤
እጅግ የተናቅህ ትሆናለህ::
3አንተ በሰንጣቃ[ሀ] ዐለት ውስጥ
የምትኖር፣
መኖሪያህንም በከፍታ ስፍራ ያደረግህ፣
ለራስህም፣
‘ማን ወደ ምድር ሊያወርደኝ ይችላል?’
የምትል፣
የልብህ ትዕቢት አታልሎሃል::
4እንደ ንስር መጥቀህ ወደ ላይ ብትወጣ፣
ጐጆህንም በከዋክብት መካከል
ብታደርግ፣
ከዚያ አወርድሃለሁ”
ይላል እግዚአብሔር::
5“ሌቦች ወደ አንተ ቢመጡ፣
ዘራፊዎችም በሌሊት ቢገቡ፣
የሚሰርቁት የሚፈልጉትን ያህል
ብቻ አይደለምን?
ወይን ለቃሚዎች ወደ አንተ ቢመጡ፣
ጥቂት ቃርሚያ አይተዉምን?
አንተ ግን ምንኛ ጥፋት ይጠብቅሃል!
6ዔሳው ግን እንዴት ተዘረፈ?
የሸሸገውስ ሀብት ምንኛ ተመዘበረ!
7ወዳጆችህ ሁሉ ወደ ድንበር ይገፉሃል፤
ጓደኞችህ ያታልሉሃል፤ ያሸንፉህማል፤
እንጀራህን የበሉ ወጥመድ ይዘረጉብሃል፤[ለ]
አንተ ግን አታውቀውም::
8“በዚያ ቀን ጥበበኞችን ከኤዶም፣
አስተዋዮችንም ከዔሳው ተራሮች
አልደመስስምን?”
ይላል እግዚአብሔር ::
9ቴማን ሆይ፤ ተዋጊዎችህ ይደነግጣሉ፤
በዔሳውም ተራሮች ያለ ሁሉ፣
ተገድሎ ይጠፋል::
10በወንድምህ በያዕቆብ ላይ ስላደረግኸው
ግፍ፣
በዕፍረት ትሸፈናለህ፤
ለዘላለምም ትጠፋለህ::

11እንግዶች ሀብቱን ዘርፈው ሲሄዱ፣
ባዕዳንም በበሮቹ ሲገቡ፣
በኢየሩሳሌምም ላይ ዕጣ ሲጣጣሉ፣
በዚያ ቀን ገለልተኛ ሆነህ ተመለከትህ፤
አንተም ከእነርሱ እንደ አንዱ ሆንህ::
12ክፉ ቀን በገጠመው ጊዜ፣
በወንድምህ ሥቃይ መደሰት
አልነበረብህም፤
በጥፋታቸው ቀን፣ የይሁዳ ሕዝብ ሲያዝኑ
ሐሤት ማድረግ አልነበረብህም፤
በጭንቀታቸውም ቀን፣
በትዕቢት ልትናገር አይገባህም ነበር::
13በጥፋታቸው ቀን፣
በሕዝቤ በር መግባት የለብህም ነበር፤
በጥፋታቸው ቀን፣
በጭንቀታቸው መደሰት
አልነበረብህም፤
በጥፋታቸው ቀን፣
ሀብታቸውን መዝረፍ አይገባህም ነበር::
14ስደተኞቻቸውን ለመግደል፣
በመንታ መንገድ መጠባበቅ አይገባህም
ነበር፣
በጭንቀታቸው ቀን፣
የተረፉትን አሳልፈህ መስጠት
አልነበረብህም::
15“በአሕዛብ ሁሉ ላይ፣
የእግዚአብሔር ቀን ደርሶአል፤
አንተ እንዳደረግኸው፣ በአንተም ላይ ይደረጋል፤
ክፉ ሥራህም በራስህ ላይ ይመለሳል::
16እናንተ በቅዱሱ ተራራዬ እንደ
ጠጣችሁ፣
አሕዛብ ሁሉ ዘወትር ይጠጣሉ፤
ይጠጣሉ፤ አብዝተውም ይጠጣሉ፤
ከዚህም በፊት እንዳልሆኑት ይሆናሉ::
17ነገር ግን በጽዮን ተራራ ነጻ መውጣት
ይሆናል፤
የያዕቆብ ቤትም እርሷ የተቀደሰች
ትሆናለች፤
ርስታቸውን ይወርሳሉ::
18የያዕቆብ ቤት እሳት፣
የዮሴፍም ቤት ነበልባል ይሆናል፤
የዔሳው ቤት ገለባ ይሆናል፤
ያቃጥሉታል፤ ይበሉታልም፤
ከዔሳው ቤት የሚተርፍ፣ አይኖርም::”
እግዚአብሔር ተናግሮአል::
19የኔጌብ ሰዎች፣

[ሀ]3 ወይም *በሴላ*
[ለ]7 የዚህ ሐረግ የዕብራይስጡ ትርጓሜ በርግጠኝነት አይታወቅም::

1፥1 ዘፍ25፥14፤ ኢሳ1፥1፤11፥14፤ 18፥2፤34፥11፤ 63፥1-6፤ኤር6፥4-5፤ 49፥7-22፤ ሕዝ25፥12-14፤ 32፥29፤ አሞ1፥11-12
1፥2 ዘኍ24፥18
1፥3 2ዜና25፥11-12፤ ኢሳ16፥1:6
1፥4 ኢዮ20፥6፤ ኢሳ10፥14፤14፥13
1፥5 ዘዳ4፥27፤ 24፥21፤ኢሳ24፥13
1፥7 መዝ41፥9፤ ኤር30፥14
1፥8 ኢዮ5፥12፤ ኢሳ29፥14
1፥9 ዘፍ36፥11:34
1፥10 መዝ137፥7፤ ሕዝ25፥12-14፤ 35፥9፤ኢል3፥19፤ አሞ1፥11-12
1፥11 ኢዮ6፥27፤ ሕዝ24፥6፤አሞ1፥6
1፥12 ኢዮ31፥29፤ መዝ137፥7፤ ምሳ17፥5፤24፥17፤ ሕዝ25፥6፤35፥15፤ ሚክ4፥11፤7፥8
1፥13 ሕዝ35፥5
1፥14 1ነገ18፥4
1፥15 ኤር46፥10፤ 50፥29፤ሕዝ30፥3፤ ኢል2፥31፤ አሞ5፥18፤ዕን2፥8
1፥16 ዘፀ15፥17፤ ኢሳ51፥17፤ ኤር25፥15፤ 49፥12፤ሰቆ4፥21-22፤ ሕዝ25፥12-14
1፥17 መዝ69፥35፤ 74፥2፤ኢሳ4፥3፤ 14፥12፤ኢል2፥32፤ አሞ9፥11-15፤ ዘካ8፥12
1፥18 ኢሳ1፥31፤ ኤር49፥10፤ ዘካ12፥6
1፥19 ዘኍ1፥36፤ ኢሳ11፥14፤ኤር31፥5

የዔሳውን ተራራ ይይዛሉ፤
ከተራራው ግርጌ ያሉ ሰዎችም፣
የፍልስጥኤማውያንን ምድር ይወርሳሉ፤
የኤፍሬምንና የሰማርያንም ዕርሻ ይይዛሉ፤
ብንያምም ገለዓድን ይወርሳል።
[20]በከነዓን ያለው ይህ የእስራኤል ስደተኞች
ወገን፣
እስከ ሰራጵታ ያለውን ምድር
ይወርሳል፤
በሰፋራድም ያሉ የኢየሩሳሌም
ስደተኞች፣
የኔጌብን ከተሞች ይወርሳሉ።
[21]የዔሳውን ተራሮች ለመግዛት፣
ነጻ አውጪዎች ወደ ጽዮን ተራራ ይወጣሉ፤
*መንግሥቱም የእግዚአብሔር ይሆናል።*

1፥20 1ነገ17፥9-10፤ኤር33፥13፤ ሉቃ4፥26 ራእ11፥15
1፥21 ዘዳ28፥29፤ መሳ3፥9፤መዝ22፥28፤ 47፥9፤ 66፥4፤ ዳን 2፥44፤ ዘካ14፥9፡16፤ ሚል1፥14፤